# የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ በጀርመን

**_Komitee zur Unterstützung der EPRP in Deutschland_**

**_Support Committee for EPRP in Germany_**

Postfach 1310 65782 Hattersheim Deutschland

## የተቃውሞ ጥሪ

## በጀርመን ሀገር ለምትገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ !!

የመለስ አገዛዝ እየተከተለ ባለው ጨቋኝ፣ ዘረኛ፣ ፀረ ዴሞክራሲ፤ ፀረ ኢትዮጵያና አምባገነን ፖሊሲው ምክንያት በሕዝባችን የተነፈገውን ይሁንታነት በአዙሪት ሁለት አሃዝ ያለው የኤኮኖሚ እድገት አስመዝግቢያለሁ በሚለው ፈሊጡ የሚያገኝ እየመሰለው ከፍተኛ የሕዝብ ኃብት በመመደብ ባለፉት ጊዜያት በስፋት የተንቀሰቃሰ መሆኑ የሚታወቅ ነው። ይህንኑ ፍላጎቱንም በይበልጥ ስኬታማ ለማድረግ ደግሞ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አፍኖ፤ ሃሳብን በነፃ የመግለፅና የመደራጀት መብቶችን ጨፍልቆ፤ የተቃዋሚ ድርጅቶች አባላትን አዋክቦ እንቅስቃሴዎቻቸውንም ገድቦና የተወሰኑትንም ሕጋዊነታቸውን ነፍጎ፤ ራሱ በራሱ ለብቻው ተወዳድሮ ላለፉት 20 አመታት እያወናበደና ሕዝብን በጎሳ እየከፋፈለ በጉልበት ከያዘው ስልጣን ላይ ለመቆየት 99.6 በመቶ የምርጫ ድምፅ አግኝቻለሁ ካለ ጀምሮ ቀድሞውኑም ለአገዛዙ አባላትና ደጋፊዎች ሕዝብን ይበልጥ ለመበዝበዝ የሚያስችላቸው ልማታዊ ዴሞክራሲ መግሥት የሚባል የማጭበርበሪያ ካባ በመደረብ ሌላ የኤኮኖሚ ዕድገትና ለውጥ የሚል የማታለያ መርሃ ግብር ቀይሶ ሕዝብን በማተራመስ ላይ ይገኛል። ይህ እንቅስቃሴውና ጥረቱ፣

- የሕዝባችንን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ከመርገጡ፣
- በርካታ ኢትዮጵያዊያንን ለአስከፊና አሰቃቂ ድህነት፣ ለእስር፣ ለተለያዩ በደሎችና ለስደት ከመዳረጉ፤
- ሀገራዊ ሉአላዊነትን የማስደፈሩና የሕዝቧንም ታሪክ የማራከሱ፤
- ሕዝባችንን በጎሳ ከመከፋፈልና፣ የሕዝብን ሀብት ከመዝረፍ ድርጊቱ፤
- በሙስና ከመጨማለቁ፣
- ሕዝባችንን አሰቃቂና አሳዛኝነቱ ወደር ከማይገኝለት የኤኮኖሚ፣ የፖለቲካና ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ ከመዝፈቁ፣
- በነፃ ገበያ ሥም የሀገሪቱን ዋና ዋና የኤኮኖሚ ተቋማት በአገዛዙ ከፍተኛ ባለሥልጣናትና ደጋፊ አባላት ሥር ከማድረጉ፣
- ገበሬውን ከቀዬው እያፈናቀለ ለምና ሰፋፊ የሆኑ የእርሻ መሬቶችን በርካሽ ዋጋ ለባዕዳኖች ከመቸብቸቡ፣
- የከተማ መሬትንም በተመሳሳይ ሁኔታ ነዋሪዎችን እያፈናቀለ ለወያኔ ሹማምንቶች ከማደሉ፣
- በረሃብ ለተጎዳው ሕዝባችን ከሚለገሰው እርዳታ፣ ለኤኮኖሚ እድገትም ሆነ ቀሳፊውን ኤድስና የወረርሽኞችን በሽታዎች ለመካለክል ተብሎ ከሚለገሰው እርዳታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በጥቂት ባለሚሎቹ የመዝረፍ ድርጊቶቹ ሁሉ ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ይህ አገዛዝ ነው እንግዲህ በሰላምና መብት እጦት፣ በመልካም አስተዳድር ጉድለት፣ በየጊዜው እያሻቀበ በሚሄደው የኑሮ ውድነት፣ ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ በበርካታ ውድ ዜጎቻችን ደብዛ መጥፋት፣ በጎጠኛና አምባገነን አገዛዙ ተማረን ከውድ ሀገራችንና ቤተሰቦቻችን

ተለይተን ለስደት የዳረገን መሆኑ የተረሳለት ይመስል አሁን ከምንኖርበት ባእድ ሀገር መጥቶ ለሕዝባችን ምንም ጠብ ባላለት የኤኮኖሚ እድገትና ለውጥ ፕሮፓጋንዳውን ሊሰብክ ተወካዮቹን በአሜሪካና በአውሮፓ ልኮ በመሯሯጥ ላይ የሚገኘው። ይህ እንቅስቃሴው የበርካታ የኢትዮጵያን ሕዝብ ስሜት ለመኮርኮርና ቀልባቸውን ለመሳብ ማንም ቀና ዜጋ የሚመኘውን የሀገር ልማትን መደገፍ ከራሱ አምባገነናዊ አገዛዝ ጋር አብሮ ያዛምድልኛል ብሎ ያሰበውን የአባይ ወንዝ የሚሌኒየም ግድብ እቅድ ይፋ ከማድረጉ ጋር ተዳምሮ እየቀረበም ይገኛል።

ይህን ይዞ ለመቅረብ ቢጥርም በራሱ ድርጊት ሙሉ እምነት እንደሌለው በቅርቡ በሰሜን አፍሪካና አካባቢዋ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመፅና በአምባገነኖች ላይ የተገኘው ድልን አስመልክቶ ከራሱ ከመለስ ጀምሮ ቱባ ቱባ ባለስልጣናቱ የሰጧቸው መግለጫዎች ያረጋግጣሉ። የሕዝባዊ አመጹና የድላቸው ወላፈኑ ወደ ኢትዮጵያም ዘልቆና የመለስ አገዛዝንም ሊለበልበው እንደማይችል በተደጋጋሚ ቢገልፅም በከፍተኛ ደረጃ እያሳሰበው መሆኑ ግን ከውስጥ አዋቂዎችና ወደ ኢትዮጵያ የሚተላለፉ የሬዲዮ ፕሮግራሞች ፍኖተ ዴሞክራሲ፤ የጀርመኑ ዶቼዌሌና የአሜሪካ ድምፅ የሚያቀርቧቸው ዜናዎች እንዳይሰሙ እያደረጋቸው ያሉት ጥረቶቹ ያሳብቁበታል።

በመሆኑም የመለስ አገዛዝ በጀርመን ሀገር በፍራንክፈርት ከተማ ለአፕሪል 16 ቀን 2011 ዓ.ም. ከ 14፡30 ጀምሮ ከታች በተጠቀሰው አድራሻ

Hörsaal H1 (Campus Bockenheim)
Goethe — Universität Frankfurt
Mertonstr, 17- 21(Eingang gegenüber Lilly Cafe
60325 Frankfurt am Main

የጠራውን ስብሰባ ቀደም ብሎ በ 13፡00 ሰአት በመገኘት በሕዝባዊ ተቃውሞ ማጋለጥና ማክሸፍ ከማንኛውም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው የሚል ፅኑ እምነት አለን። በበኩላችን አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ላይም እንገኛለን። ይህን የመሰለ ተግባርም በሀገር ቤት ያሉ ዜጎቻችን ከኛ የሚጠብቁት እንደሆንም ጥርጥር የለንም። ስለሆነም በጀርመን ሀገር የምንገኝ ሀገር ወዳዶች በሙሉ በተባለው ቦታ በመገኘት በሕዝባችን ላይ እየደረሰ ያለውን በደል እስራትና ግድያ፣ ጭቆናና መብት አልባ መሆንን በማጋለጥ ለወያኔ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ አለመሆናችንን በቦታው በመገኘት እንድናረጋግጥ ይህን ሕዝባዊ ጥሪ እናቀርባለን። በአሜሪካ የሚኖሩ የትግል አጋሮቻችን ተመሳሳይ ጥረት እያደርጉ ናቸውና ከነሱም ጎን በመሆንና ትግላችንን አለም አቀፍ ገፅታ በመስጠት ለሕዝባችን ያለንን ፍቅርና ከበሬታ በተግባር ለአለም ሕዝብ እናሳይ። ይህ አይናችሁን ጨፍኑና ላሞኛችሁ ጥሪውን እናክሽፍበት። ጊዜው ይርዘምም ይጠርም የኢትዮጵያ ህዝብ ለወሳኝ ድሉ መነሳቱ የማይቀር መሆኑን በመረዳት ከጎኑ እንቁምለት። ከጫንቃው ላይ የተቆናጠጠውን አምባገነን አገዛዝ አሻፈረኝ፣ እምቢኝ በማለት የተቃውሞ ድምፃችንን እናሰማ እንላለን። የመጪው ወሳኝ ትግል አጋር መሆናችንንም ከወዲሁ በተግባር እናስመስክር።

በጋራና በተባበረ ትግል የመለስ አምባገነን አገዛዝን እናስወግድ!!
የሥቃይ፣ የበደልና ሕዝብ ከፋፋይ ሥርአት መልዕክተኞችን ወጊዱ እንበላቸው!!
የወንጀለኛ አስተባባሪ፤ ተባባሪ ተንኮል ይከሽፋል!!
ለግንኙነት በሚከተለው ስልክ 0173 42 12 622 ይደውሉ።
በጀርመን የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ